Hallo
Basel-Stadt

Kanton Basel-Stadt

# የኑሮ አጋርነት እና ልጆች


አጋርነት
የወላጆች መብት እና ግዴታ
ወላጅ መሆን
የሕፃናት ልጆች እንክብካቤ
የቤተሰብ ዳግም መቀላቀል ፕሮግራም
ግጭቶች

# አጋርነት

ስዊዘርላንድ ውስጥ የተለያዩ ሰዎች በጋራ በአንድ ላይ ይኖራሉ። መጋባት ከፈለጉ ግን ዕድሜቻቸው ቢያንስ ቢያንስ 18 መሙላት አለበት። ሁለቱም የትዳር ጓደኞማቾች እኩል መብት አላቸው።

## በጋራ አንድ ላይ መኖር

ስዊዘርላንድ ባለፉት 10 ዓመታት ብዙ ለውጥ አሳይታለች። አብዛኛውን ግዜ ያልተጋቡ ጥንዶች (ሳይጋቡ እንደ ትዳር አብሮ መኖር፣ Konkubinat). በጋራ አንድ ላይ ይኖራሉ። ጥንዶቹ የጋራ ልጆች አላቸው። በጥንዶቹ/በአጋሮቹ/ መካከል ቋሚ የሆነ የስራ ክፍፍልና ድርሻ የለም። ይህም ማለት ሴቶችና ወንዶች ግንኙነታቸውን በሚመለከት የነጠረ የስራ ክፍፍልና ድርሻ የላቸውም፣ ይህም ማለት እነዚህ ሴቶች እና ወንዶች በግንኙነታቸው ውስጥ የተወሰኑ የስራ ክፍፍልና ድርሻ ማከናወን አያስፈልጋቸውም።
ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ጥንዶች በጋራ በአንድ ላይ መኖር ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ አንድ ወንድ ከአንድ ወንድ ጋር፣ ወይም አንዷት ሴት ከአንዷት ሴት ጋር ማለት ነው። እነሱም እንደ ሌሎች ጥንዶች እኩል መብት አላቸው፣ ከዚያም በላይ መጋባትም ይፈቀድላቸዋል።

## ጋብቻ

ስዊዘርላንድ ውስጥ 18 ዓመት ዕድሜ የሞላው ሰው ነው ማግባት የሚፈቀድለት። ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ስዎችም ማጋባት ይችላሉ። አንድ ወንድ ከአንድ ወንድ ጋር፣ እንደዚሁም አንዷት ሴት ከአንዷት ሴት ጋር መጋባት ይችላሉ። እነሱም እንደ ሌሎች ጥንዶች እኩል መብት አላቸው፣ በዚህም ምክንያት መጋባትም ይፈቀድላቸዋል። መጋባት በሚፈልጉበት ግዜ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ማለትም /በሲቪል ማዘጋጃ ቤት/ Basel-Stadt (Zivilstandsamt) ማመልከት አለባቸው። የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ የአሰራር ሂደቱን የሚጀምረው (Ehevorbereitungsverfahren)“በጋብቻ ዝግጅት ሂደት“ መሰረት ነው። በዚህ የአሰራር ሂደት ጋብቻው መስመር እንዲይዝ ይደረጋል። ለምሳሌ ያህል ጽ/ቤቱ ሁለቱ ጥንዶች ለመጋባት መስፈርቱን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል። የአሰራር ሂደቱ ሲያልቅ ጥንዶቹ በ3 ወራት ውስጥ መጋባት አለባቸው። የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ የአሰራር ሂደቱ እንዴት እንደሆነ እና ምን ዓይነት ሰነዶች እንደሚያስፈልጉ መረጃ ይሰጣቸዋል።
ምናልባት አንዳቸው ነዋሪነታቸው ውጪ አገር ከሆነ መጀመሪያ ወደ ስዊዘርላንድ መግባት እንዲፈቀድላቸው ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው (ለመጋባት የሚደረጉ ዝግጅቶች) ። ከዛ በኋላ ሁለቱም እዚህ ስዊዘርላንድ ውስጥ መጋባት ይችላሉ።
የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ የይስሙላ ጋብቻ (Scheinehe) ነው ብሎ ጥርጣሬ ሊያድርበት ይችላል። የይስሙላ ጋብቻ (Scheinehe) ማለት: ሁለቱ ጋብቻውን የሚፈጽሙት አንዳቸው ስዊዘርላንድ ውስጥ መኖር እንዲያስችላቸው ብቻ ከሆነ ነው። በዚህም የተነሳ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ ጋብቻውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። ጋብቻውን ፈጽመው ከሆነም ጽ/ቤቱ ጋብቻውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። ይህም ማለት ጋብቻው ይፈርሳል ማለት ነው። ምናልባትም በዚህ በይስሙላ ጋብቻ ምክንያት የመቆያ/የመኖሪያ ፍቃዳቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

## መብት እና ግዴታዎች

ሁለቱም ባለትዳሮች ተመሳሳይ መብት እና ግዴታዎች አላቸው፣ ይህም በሕግ ላይ በሰፈረው መሰረት ነው። በትዳራቸው ውስጥ እኩል መብት አላቸው። ሁለቱም የትዳር አጋሮች ፈቅደው መጋባት አለባቸው። የግዴታ ጋብቻ (Zwangsheirat) ማለት አንድ ሰው ተገዶ ጋብቻ ሲፈጽም ነው። አስተዳደሩ ይህ እንዳልሆነ ሲያረጋግጥ፣ ትዳሩን ውድቅ ያደርገዋል። አንድ ሰው ሌላውን ሰው በማስገደድ ጋብቻ ፈጽሞ ከሆነ በሕጉ መሰረት ይቀጣል። ተገድደው ያለ ፍቃድዎ ጋብቻ ውስጥ የሚገቡ ሆነው ይሰማዎታል? Beratungsstelle zwangsheirat.ch የሚባለው የግዴታ ጋብቻን በሚመለከት የምክር አገልግሎት የሚሰጠው ተቋም ድጋፍ ያደርግሎታል። በነጻ ስልክ መደወል ይችላሉ፣ አያስከፍልም። የቴለፎን ቁጥሩ እንደሚከተለው ነው፣ 0800 800 007

## የቤተሰብ እቅድ

ስለ ቤተሰብ እቅድ በሚመለከት ጥያቄ አለዎት፣ ማለትም ስለ እርግዝና እና ስለ ጾታ? ይህንን በሚመለከት በ Basel-Stadt ካንቶን የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮዎች አሉ። እነዚህ ቢሮዎች ስለተለያዩ አርእስቶች፣ ለምሳሌ ያህል ስለ ጽንስ መከላከያ፣ ስለ ጾታዊ ችግሮች፣ ስለ ጾታዊ ጤንነት እንክብካቤ፣ ስለ አባለዘር በሽታዎች ወይም ያለ ፍላጎት ስለማርገዝ መረጃ ይሰጣሉ። ልጅ ለመውለድ እየጠበቁ ከሆነ ወይም ልጅ ወልደው ከሆነ ምክር ይለግስዎታል።

## ፍቺ

ባለ ትዳር ነዎት እናም ፍቺ መፈጸም ይፈልጋሉ? የሚፈልጉ ከሆነ ባዝል ከተማ በሲቪል ፍርድ ቤት Basel-Stadt (Zivilgericht) የፍቺ ማመልከቻዎን ማቅረብ አለብዎት። ፍቺውን ብቻዎትን ማቅረብ ይችላሉ፣ ወይም ከትዳር ጓደኛዎ ጋር አንድ ላይ በጋራ ያመልክቱ።
ውጭ አገር ነው የተጋቡት? ቢሆንም እንኳን በስዊዘርላንድ ሕግ መሰረት መፋታት ይችላሉ። ነገር ግን ቢያንስ ከአንድ ዓመት በላይ ስዊዘርላንድ ውስጥ መኖር አለብዎት፣ ከዛ በተጨማሪም ዋና መኖሪያዎ ስዊዘርላንድ ውስጥ መሆን አለበት። ከተፋቱ በፍቺው ምክንያት ምናልባትም መኖሪያ ፍቃድዎ ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ምናልባትም ከፍቺው በኋላ ስዊዘርላንድ መኖር ሊፈቀድልዎ አይችልም ይሆናል። ዜግነት መውሰድ ይፈልጋሉ? ምናልባትም ከፍቺው በኋላ የስዊዘርላንድ ዜጋ መሆን አይችሉ ይሆናል።
ከፍቺው በኋላ ስዊዘርላንድ መቆየት ይፈቀድሎታል? የጋብቻ እና የቤተሰብ የምክር አገልግሎት ጽ/ቤት ምክር ቢጠይቁ መልካም ነው። የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ፣ ይህንን በሚመለከት ልዩ ሕጎች አሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/partnerschaft

# የወላጆች መብት እና ግዴታ

**ልጅ እንደወለዱ ወድያውኑ በነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ልጅዎን ማስመዝገብ አለብዎት። ያገቡ ከሆነ የልጁን የማሳደግ መብት በሚመለከት በሕጉ ላይ በትክክል የተቀመጠ ነው። ነገር ግን ያላገቡ ከሆኑ የልጁን የማሳደግ መብት በሚመለከት በግልዎ መብትዎን ማስከበር አለብዎት።**

## የወሊድ ምዝገባ

የወለዷቸውን ልጆች ሁሉንም በነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት (Zivilstandsamt) ማስመዝገብ አለብዎት። ማሳሰቢያ: ልጅዎ በተወለደበት ቦታ ባለው የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ሄደው ልጅዎን ማስመዝገብ አለብዎት። ምናልባትም ወደ መኖሪያዎ ወዳለው የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ቢሮ መሄድ ላያስፈልጎት ይሆናል።

ልጅዎ ሆስፒታል ከሆነ የተወለደው:

ሆስፒታሉ ሰነዱን ወደ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት በቀጣይነት ይልከዋል። ይህም ማለት እርስዎ ምንም ማድረግ አይጠበቅብዎትም።

ልጅዎ ሆስፒታል ካልሆነ የተወለደው:

ልጅዎ የተወለደው ምናልባት ቤት ውስጥ ወይም ሌላ ቦታ ሊሆን ይችላል፣ ይህ ከሆነ ልጅዎን በአካል የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ያስመዝግቡት። ለማስመዝገብ 3 ቀን ይሰጥዎታል። የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ ለምዝገባው ማቅረብ ያለብዎትን ሰነዶች ይነግርዎታል።

ማወቅ ያለብዎት መረጃ፣

ስዊዘርላንድ የተወለደ ልጅ ስዊዘርላንድ ስለተወለደ ብቻ ዜጋ አይሆንም። ወዲያውኑ የስዊዘርላንድ ዜግነት አይሰጠውም።

## የአባትነት ዕውቅና ማረጋገጫ

አግብተው በትዳር ልጅ ወልደዋል:

ባልየው ወዲያውኑ በቀጥታ አባት መሆኑ ይመዘገባል። ምናልባት አባትየው አባት መሆኑን ከተጠራጠረ፣ ፍርድ ቤት መሄድ ይችላል እናም አባትነቱን መካድ ይችላል።

ሳይገቡ ልጅ ወልደዋል:

ባልየው ወዲያውኑ በቀጥታ አባት መሆኑ አይመዘገብም። ልጁ ከመወልዱ በፊት ወይም ከተወለደ በኋላ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት በመሄድ አባት መሆኑ ዕውቅና እንዲሰጠው ማድረግ ይችላል። ምናልባት አባትየው የተወለደው ልጅ፣ ልጁ መሆኑን ዕውቅና ላይሰጠው ይችላል። ይህ በሚሆንበት ግዜ የልጁ እናት ፍርድ ቤት ሄዳ አባትየው ልጁ መሆኑን እንዲቀበለው ማመልከት ትችላለች።

## የወላጅ ሃላፊነት

እንደ ወላጅ መጠን ወላጆች የልጆቻቸውን ደህንነት በሚመለከት ሃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው። ይህም መብትና ግዴታቸው ነው (የወላጅ ሃላፊነት፣ elterliche Sorge) ። ለምሳሌ ያህል ልጆቻቸውን ማስተማርና፣ ለልጆቻቸው ህይወት የሚያስፈልገውን ተገቢውን ክፍያ መፈጸም አለባቸው። በተጨማሪም በሕጉ መሰረት ልጆቻቸው 18 ዓመት ዕድሜ እስኪሞላቸው ድረስ፣ ልጆቻቸውን መወከልን የልጆቻቸው ተጠሪ መሆን አለባቸው።

ተጋብታችሁ ከሆነ፣

ተጋብታችሁ ከሆነ ልጆቻችሁን በጋር ለማሳደግ ሁለታችሁም እኩል መብት እና ሃላፊነት አለባችሁ።

ያልተጋባችሁ ከሆነ፣

አስቀድሞ አባትየው ልጁ መሆኑን ዕውቅና መስጠት አለበት። ከዚያ በመቀጠልም ሁለቱም ተስማምተው በጋራ ልጃቸውን ለማሳደግ መወሰናቸውን (gemeinsame elterliche Sorge). በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው። ከዚያ በፊት ግን አባትየው ልጁን በነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ለልጁ ዕውቅና መስጠት አለበት። ሌላው አማራጭ፣ ከዚያ በኋላ ቆይተው ወደ ህጻናት ደህንነት ጥበቃ ጽ/ቤት (Kindesschutzbehörde, KESB) መሄድ ይችላሉ።.

በጋራ ልጃችሁን ለማሳደግ ስምምነት ላይ ካልደረሳችሁ ግን የህጻናት ደህንነት ጥበቃ ጽ/ቤት ውሳኔውን ይሰጣል።.

ይህንን በሚመለከት ጥያቄ ካለዎት ወይም እርዳታ የሚያስፈልጎት ከሆነ፣ ወደ የቤተሰብ የምክር አገልግሎት ጽ/ቤት በመሄድ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ቀለብ

ተለያይታችሁ የምትኖሩ ከሆነ፣ ይህም ቢሆንም እንኳን ሁለታችሁም በቀጣይነት ልጃችሁን መንከባከብ አለባችሁ። ማን ልጁን እንደሚያሳድግና እንደሚንከባከብ እና ማን ምን ያክል ገንዘብ እንደሚከፍል (ቀለብ፣ Unterhalt).መስማማት አለባችሁ።

ለልጃችሁ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ቀለብ ሁለታችሁም ነው የምትከፍሉት። ምናልባት አንዱ ወላጅ ከሌላው ወላጅ የበለጠ ወይም ያነሰ መክፈል ሊኖርበት ይችላል። ወይም በጭራሽ ላይከፍሉም ይችላሉ። ምን ያህል ገንዘብ ደመወዝ እንደሚያገኙ እና ልጁን ምን ያህል እንደሚንከባከቡት፣ በሚንከባከቡት መጠን ይወሰናል። ወላጆቹ አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር ክፍያውን በሚመለከትስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ፣ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላሉ።

ከወላጆቹ አንዱ መክፈል ያለበትን ድርሻውን ካልከፈለ፣

ከወላጆቹ አንዱ ለልጁ ማሳደጊያ የሚሆን መክፈል ያለበትን ድርሻውን ካልከፈለ፣ የመኖሪያችሁን ኮሙዩን ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። የመኖሪያችሁ ኮሙዩን ገንዘቡን እንዲሰጥዎት ይረዳዎታል። ገንዘቡ የሚገባዎት ከሆነ፣ ምናልባት ለቀለብ መሸፈኛ እንዲጠቀሙበት ሊሰጥዎት ይችላሉ። ይህም አቅርቦት በቅድሚያ በብድር መልክ ለቀለብ የሚሰጥ ሆኖ በኋላ የሚተካ/የሚቀነስ/ ነው። ይህም Alimentenbevorschussung.ተብሎ ይጠራል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/rechte-und-pflichten-der-eltern

# ወላጅ መሆን

ልጅ ማሳደግ ቀላል አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ምናልባት ለልጅዎ ምንድነው የበለጠ ጥሩ የሚሆነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ከሌሎች ወላጆች ጋር ስለ ጉዳዩ ማውራት በጣም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የተለያዩ የምክር አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤቶች ሊረዱዎት ይችላሉ።

## መገናኛ ማዕከላት

ለእናቶችና ለአባቶች ተብለው የተዘጋጁ ብዙ አቅርቦቶች አሉ። እዚህ ከሌሎች ወላጆች ጋር መነጋገር ወይም ከልጆችዎ ጋር በአንድ ላይ አንድ ነገር ማድረግ ይችላሉ።

- ዳዴ የሚሉ የሕጻናት ግሩፖች (Krabbelgruppen) ለሕጻናቶች እና ዕድሜያቸው እስከ 2 አመት ድረስ ለሆኑ ለትንሽ ልጆች ናቸው። በዛውም ከሌሎች ወላጆች ጋር እንዲተዋወቁ ያስችሎታል።
- የወላጆች እና የልጆች ጅምናስቲክ (MuKi-ጅምናስቲክ፣ VaKi-ጅምናስቲክ ወይም ElKi-ጅምናስቲክ) ፣ ወላጆች ከትንሽ ልጆች ጋር ነው። እርስዎም አብረው መጫወት፣ መንቀሳቀስ እና መዝናናት ይችላሉ። ብዙዎቹ ኮምዩኖች የጅምናስቲክ አቅርቦት አላቸው።
- የመኖሪያዎ የመገናኛ ማዕከለት (Quartiertreffpunkte) ብዙ የተለያዩ ፕሮግራሞች ለወላጆችና ለልጆች አሏቸው።
- ቤተ መጻህፍት እና ቤተ አሻንጉሊት ለትናንሾች እና ለትላልቅ ልጆች እንዲሁም ለወላጆች ብዙ አቅርቦቶች አሏቸው።

## ትምህርት ለወላጆች

በBasel-Stadt በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለወላጆች የሚሰጡ ኮርሶች አሉ። ለስደተኞችም እንዲሁ የተለዩ ኮርሶች አሉ። ለምሳሌ ያህል ስለ ስዊዘርላንድ የትምህርት ስርዓት እና እንዲሁም በሌላ ቋንቋ የሚሰጡ ኮርሶችም አሉ።

## ትምህርታዊ ምክር

ስለ ልጆችዎ ትምህርት ጥያቄዎች ካለዎት፣ ብዙ የተለያዩ የምክር አገልግሎት ጽ/ቤቶች ያግዝዎታል።

ለምሳሌ ያህል የሕጻናቶች እና ዕድሜያቸው እስከ 5 ዓመት የደረሱ ትናንሽ ልጆች በሚመለከት ወደ የወላጆች የምክር አገልግሎት ቢሮ (Elternberatung) ይሂዱ።

አስቸኳይ ጥያቄዎች ካሉዎት ወደ የወላጆች የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል ይችላሉ። እዛም ከባለሙያዎች የምክር አገልግሎት ያገኛሉ። በሚደውሉበት ግዜ መደበኛ የቤት ስልክ ክፍያ ነው የሚከፍሉት። ቴለፎን፣ 0848 35 45 55 ይደውሉ ወይም በኢ-ሜል ይጻፉ። አድራሻውን በ www.elternnotruf.ch. ድረ ገጽ ላይ ያገኛሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/eltern-sein

# የሕፃናት ልጆች እንክብካቤ

ብዙ አባቶች እና እናቶች ልጅ ወልደውም እንኳን ቢሆን ስራ ይሰራሉ። ለዚህም ነው በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ ለህጻናት እንክብካቤ ልዩ አቅርቦቶች ያሉት። አብዛኛዎቹ አቅርቦቶች ክፍያ ያስከፍላሉ።

## የልጆች የቀን እንክብካቤ ማዕከላት

በልጆች የቀን እንክብካቤ ማዕከላት ልጅዎት ቀኑን ሙሉ እንክብካቤ ይደረግለታል። የልጆች የቀን እንክብካቤ ማዕከላት በምህጻረ -ቃል Kita ይባላሉ። ብዙዎቹ Kita'ዎች ከ3 ወራት እስከ ለትምህርት የደረሱ ልጆች የሚውሉበት ነው። በተጨማሪም አንዳንድ Kita'ዎች ትምህርት ለጀመሩ ሕጻናት ከትምህርት ቤት በፊት፣ በምሳ ሰዓት እንዲሁም ከትምህርት በኋላም ይንከባከባሉ።
ልጅዎን በጣም ቀደም ብለው ማስመዝገብ አለብዎት፣ አለበለዚያ ግን ወረፋው በጣም ረጅም ነው። የKita'ዎች የክፍያ ዋጋ የተለያየ ነው። የሚኖሩበት ኮምዩን ለአንዳንድ Kita'ዎች ወጪዎችን በከፊል ይሸፍናሉ። Kita'ዎች እና የሚኖሩበትን ኮምዩን Kita ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጣ እና ልጅዎን እንዴት እንደሚያስመዘግቡ መጠየቅ ይችላሉ።

## የጨዋታ ቡድኖች

ብዙ ልጆች ትምህርት ቤት ከመጀመራቸው በፊት የጨዋታ ቡድኖችን ይሳተፋሉ (Spielgruppe)። በጨዋታ ቡድን ውስጥ ከ3 ዓመት እድሜ ጀምሮ ያሉ ልጆች ያለ ወላጆቻቸው ተገናኝተው ይጫወታሉ።. በሙያ የሰለጠኑ ተንከባካቢዎች ልጆቹን ጨዋታ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያግዟቸዋል። ልጆቹ መገጣጠም እና መጫወት ለምሳሌ አብረው በአንድ ላይ በመጫወቻ ቡድኑ ለመጫወት በፈቃደኝነት ነው። ልጅዎት ቤት ውስጥ ጀርመንኛ አይናገርም? እዚያም በጨዋታ ቡድን ውስጥ ጀርመንኛ መማር እንዲጀምር ጥሩ አጋጣሚ ነው። ይህም ልጅዎ ትምህርት ሲጀምር እንዲቀለው ያደርገዋል።

## ዕለታዊ ፕሮግራሞች / ምሳ

በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃዎች እና ሁለተኛ ደረጃዎች ውስጥ በትምህርት ቤት ሕንፃ ውስጥ ወይም በጣም ቅርብ አካባቢ. ዕለታዊ ፕሮግራሞች (Tagesstrukturen) ይካሄዳሉ። ዕለታዊ ፕሮግራሞች ማለት ልጆቹ በምሳ ሰአት ትምህርት ቤት ይቆያሉ እናም ምሳ ይሰጣቸዋል። ከት/ቤት በኋላ ልጆቹን የሚንከባከባቸው ሰው ይኖራል፣ እዛም ልጆቹ የቤት ስራቸውን ሊሰሩ ይችላሉ።.

## በቀን ህጻን ተንከባካቢ ቤተሰቦች

ልጅዎን በቀን ህጻን ተንከባካቢ ቤተሰቦች እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ማድረግ ይችላሉ። በቀን ህጻን ተንከባካቢ ቤተሰቦች (Tagesfamilie) ማለት እንደ ቤተሰብ ሆነው ቀኑን ሙሉ ልጅን የሚንከባከቡ ወይም ከትምህርት ቤት በኋላ ቤታቸው በመውሰድ ልጅን የሚንከባከቡ ናቸው። አገናኝ /አቅራቢ/ ቢሮዎች ለርሶ የሚስማማ የቀን ህጻን ተንከባካቢ ቤተሰብ በመፈለግ ይረዱዋችኋል። እነዚህ አገናኝ ቢሮዎች አንድ የቀን ህጻን ተንከባካቢ ቤተሰብ ምን ያህል እንደሚያስከፍሉ መረጃ ይሰጥዎታል።

## የሕፃናት ተንከባካቢ / ድንገተኛ ሁኔታዎች

ስዊዘርላንድ በማታ ወይም በሳምንቱ መጨረሻ ወጣቶች የሕፃናትን የመንከባከብ ስራ ይሰራሉ። ወጣቶቹ ለስራውም ይከፈላቸዋል። የስዊዘርላንድ ቀይ መስቀል ማህበር Basel-Stadt (SRK) የሕፃናት ተንከባካቢ የሚያገናኙ አቅራቢ ቢሮዎች የስም ዝርዝር አለው። እነሱም የእንክብካቤ ኮርስ የወሰዱ ናቸው።

በድንገተኛ ሁኔታ ወቅት የሕጻናት እንክብካቤ፣
ምናልባት ድንገተኛ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል እና እርስዎም በአስቸኳይ ልጅዎትን የሚንከባከብሎት ሰው ይፈልጉ ይሆናል። ለምሳሌ ያህል፣ እርስዎ ወይም አጋርዎ ሆስፒታል መሄድ ያስፈልጎት ይሆናል፣ ሆኖም ግን ልጅዎን የሚንከባከብሎት ሰው ላይኖር ይችላል። በዚህ ግዜ የስዊዘርላንድ ቀይ መስቀል ማህበር Basel-Stadt (SRK) በድንገተኛ ሁኔታ ወቅት የሕጻናት እንክብካቤ ያደርጋል። እንክብካቤውም በክፍያ ነው። ነገር ግን አንዳንድ የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ወጪውን ይሸፍናሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/kinderbetreuung

# የቤተሰብ ዳግም መቀላቀል ፕሮግራም

ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ የቤተሰብዎ አባላቶች ወደ ስዊዘርላንድ ሊመጡ ይችላሉ። ይህ እንዲሆን መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች አሉ። ስዊዘርላንድ ዘመዶችዎ ወይም ጓደኞችዎ እንዲጎበኙዎት ይፈልጋሉ? ከፈለጉ አንዳንድ ጊዜ ለመግቢያ ቪዛ ማመልከት አለባቸው።. ይህም ከየትኛው አገር ጎብኚዎት የሚመጡ መሆኑ ነው የሚወስነው።

## የቤተሰብ ዳግም መቀላቀል ፕሮግራም

እዚህ የሚኖሩ ከሆነ፣ ምናልባት የቅርብ ዘመዶችዎን ወይም የትዳር ጓደኛዎን ወደ ስዊዘርላንድ (በቤተሰብዎ ዳግም መቀላቀል ፕሮግራም፣ Familiennachzug) ማምጣት ይችሉ ይሆናል። ለየትኛው የቤተስብዎ አባል ማመልከቻ ማቅረብ ይፈቀድሎታል? ወሳኙ ዜግነትዎ ወይም ምን ዓይነት የመኖሪያ ፈቃድ እንዳለዎት ነው። በግዝያዊነት የመቆያ ፍቃድ ብቻ የተመዘገቡ ከሆነና ማለትም F መታወቂያ የተሰጠዎት ከሆነ፣ ምናልባትም ቤተሰብዎ ተከትለዎት መምጣት ይፈቀድላቸው ይሆናል።
ቤተሰብዎ ከእርስዎ ጋር መቀላቀል ይችሉ እንደሆነ የሚወስነው የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) ነው። የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት በቀጣይነት ምን ማድረግ እንዳለብዎት እና እንዲሁም ምን ዓይነት ሰነድ እንደሚያስፈልጎት ተገቢውን መረጃ ይሰጥዎታል።
ማሳሰቢያ፣
ቤተሰብዎ ዳግም ከእርስዎ ጋር መቀላቀል እንዲችሉ በተሰጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ማመልከት አለብዎት። ለልጆች ከሆነ ገደቡ ከአዋቂዎች ያንሳል፣ ለምሳሌ የትዳር ጓደኛዎን ለማምጣት።

## ለጋብቻ ዝግጅት

ስዊዘርላንድ ነው የሚኖሩት እናም ከውጪ አገር ሰው ማግባት ይፈልጋሉ? የመግቢያ ፈቃድ ስለሚያስፈልግ አስቀድሞ ማመልከት ያስፈልጋል፣ ከጋብቻ ዝግጅት ሂደት አካል አንዱ ነው። (Vorbereitung der Heirat). በዚህም አጋርዎ ከመጋባታችሁ በፊት ካሉበት አገር ወደ ስዊዘርላንድ መግባት ያስችላቸዋል፣ በመቀጠልም እዚህ መጋባት ትችላላችሁ።
አጋርዎ የመግቢያ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚወስነው የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) ነው። የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት በቀጣይነት ምን ማድረግ እንዳለብዎት እና እንዲሁም ምን ዓይነት ሰነድ እንደሚያስፈልጎት ተገቢውን መረጃ ይሰጥዎታል።

## የመግቢያ ቪዛ

ዘመድዎ ወይም ጓደኞችዎ ከትውልድ አገርዎ እርስዎን ሊጎበኙዎት /ሊጠይቆት/ ወደ ስዊዘርላንድ መምጣት ይፈልጋሉ?
የሚፈልጉ ከሆነ ወደ ስዊዘርላንድ የመግቢያ ቪዛ ያስፈልጋቸዋል። አብዛኛውን ግዜ የመግቢያ ቪዛ ለማግኘት ቀላል አይደለም። አንዳንድ ግዜ እርስዎ የጋበዟቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የግብዣ ወረቀት ማሳየት አለባቸው። ወይም ጎብኚዎቹ ራሳቸውን ፋይናንስ ለማድረግ ዓቅም ያላቸው መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው። (ግዴታ የሚያስገባ ውል፣ Verpflichtungserklärung).
ውጭ አገር የሚገኘው የስዊዘርላንድ ኢምባሲ ቪዛ መሰጠት እንዳለበት ይወስናል። ኢምባሲው ጎብኚዎች በቀጣይነት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና እንዲሁም ምን ዓይነት ሰነድ እንደሚያስፈልጋቸው ተገቢውን መረጃ ይሰጣል። እንዲሁም ከስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/familiennachzug

# ግጭቶች

በቤተሰብ ወይም በጓደኞች መካከል ግጭት እና ጥል አለ? ካለ የተለያዩ የምክር አገልግሎት ሰጪ ጽ/ቤቶች በቀጣይነት ሊያግዝዎት ይችላሉ። በቤተሰብ ውስጥ እና በትዳር ጓደኛማቾች መካከል ጥቃት መፈጸም ክልክል ነው። "ሄሎ ባዝል ከተማ" ላይ የቤት ውስጥ ጥቃትን በሚመለከት ራሱን የቻለ አርእስት ተሰጥቶታል። እዛም ይህንን አርእስት በሚመለከት በቂ መረጃ ያገኛሉ።

## በጓደኞች መካከል ግጭት

ከአጋርዎ ጋር ችግር ካለብዎት የሰለጠኑ ባለሙያዎች እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። (የትዳር የምክር አገልግሎት ማዕከል፣ Eheberatung). መፍትሄዎችን ለማግኘት ከእርስዎ ጋር አብረው የሚሰሩ ልዩ የምክር አገልግሎት ማዕከላት አሉ። አብዛኛውን ግዜ የመጀመሪያው ንግግር ነጻ ነው፣ ወይም ትንሽ ነው የሚያስከፍለው።

## በቤተሰብ መካከል ግጭት

ልጆች ካለዎት፣ አልፎ አልፎ ከባድ የሆኑ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ይህም ለወላጆችና ለልጆች ውጥረት ይፈጥርባቸዋል። በቀጣይነት መፍትሔ ለማግኘት ከተቸገሩ እርዳታ መጠየቅ ከሁሉም የተሻለ ነው።
እርዳታ ለወላጆች፣

- የቤተሰብ የምክር አገልግሎት ማዕከል (Familienberatungsstelle) በግልዎ የምክር አገልግሎት ያገኛሉ።
- ስለ ልጅ አስተዳደግ ጥያቄዎች ካለዎት ወይም የልጆችዎ ሁኔታ የሚያሳስብዎት ከሆነ፣ የወላጆች ድንገተኛ ስልክ አገልግሎት ጥሪ ይጠቀሙ። በሰለጠኑ ባለሙያዎች የምክር አገልግሎት ያገኛሉ፣ በስልክ ቁጥር 0848 35 45 55 ይደውሉ /መደበኛ የቤት ስልክ ክፍያ ነው የሚከፍሉት/ ወይም ኢ-ሜይል ይጻፉ።

ለልጆችና ለወጣቶች፣

- ልጆችና ወጣቶች የአደጋ ጊዜ ቁጥር መደወል ይችላሉ። ኢ-ሜይል ወይም የአጭር ጽሑፍ መልዕክት ይጻፉ፣ ወይም ቻት ያድርጉ። ቴለፎን 147 ይደውሉ (የነጻ ስልክ ነው).

## የቤት ውስጥ ጥቃት

በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ኦፊሻል የሆነ ወንጀል ነው፣ በዚህም የተነሳ ክልክል ነው። አንድ ሰው ጥቃት ከፈጸመ፣ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል። ማንኛውም ዓይነት ጥቃት የተከለከለ ነው። ማንም ሰው በቤተሰቡ ውስጥ ባሉ ሌሎች ሰዎች፣ በትዳር አጋር ላይ ወይም በልጆች ላይ የኃይል እርምጃ መውሰድ አይችልም። ባለስልጣን ጽ/ቤቶች የቤት ውስጥ ጥቃት መፈጸሙን ካረጋገጡ፣ ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ አለባቸው።
ቤተስብ ውስጥ ጥቃት ይደርስብዎታል? እርዳታ የት ማግኘት እንደሚችሉ የሚጠቁሙ አቅርቦቶች አሉ። አቅርቦቶቹ ከክፍያ ነጻ ናቸው እናም በሚስጥርም የተጠበቁ ናቸው።

- Frauenhaus / Väterhaus: ሴቶች ወይም ወንዶች ጥቃት በሚደርስባቸው ግዜ፣ ለተወሰነ ግዜ የሴቶች መጠለያ ወይም የወንዶች መጠለያ ውስጥ መኖር ይችላሉ። ከልጆችዎ ጋራ በአንድ ላይ ከለላ መፈለግ ይችላሉ። ሴቶች በሴቶች መጠለያ ቀንና ለሊት በስልክ ቁጥር 061 681 66 33 መደወል ይችላሉ።

- የልጆች የአደጋ ጊዜ ጥሪ፣ ልጆችና ወጣቶች የአደጋ ጊዜ ቁጥር መደወል ይችላሉ። ቴለፎን 147 በነጻ መደወል ይችላሉ።
- ከቤተሰብ አባላትዎ ውስጥ ከአንዳቸው ስጋት እንዳለዎት ይሰማዎታል? ከተሰማዎት በቴለፎን ቁጥር 117 ፖሊስ ይደውሉ። ፖሊስ ጥቃት ፈጻሚውን ከአፓርታማው ወይም ከቤቱ ረዘም ላለ ጊዜ ማስወጣት ይችላል። ጥቃት ፈጻሚው ወደ አፓርታማ ወይም ቤት ውስጥ እንዲገባ አይፈቀድለትም።

"ሄሎ ባዝል ከተማ" ላይ የቤት ውስጥ ጥቃትን በሚመለከት ራሱን የቻለ አርእስት ተሰጥቶታል። እዛም ይህንን አርእስት በሚመለከት በቂ መረጃ ያገኛሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/konflikte